# የ MEMORIAL HERMANN HEALTH SYSTEM ፖሊሲ

**የፖሊሲ አርእስት:** የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ

**የታተመበት ቀን:** 12/19/2017
**እትም:** 4

---

**የፖሊሲ አላማ:**

Memorial Hermann Health System (“MHHS”) የ Harris፣ Montgomery፣ Fort Bend እና ሌሎች በአካባቢው የሚገኙ 501(c)(3) ካውንቲዎችን የሚያገለግሉ የውስጣዊ ገቢ ኮድ ክፍል ሆስፒታሎችን ያስተዳድራል። MHHS ግለሰቦች የመክፈል አቅማቸው ምንም ይሁን ምን ከግምት ሳናስገባ እንዲሁም ያለ ምንም አድልዎ፣ መድህን የሌላቸው እንዲሁም ከበቂ በታች የመድህን ሽፋን ያላቸው ሆነው አስቸኳይ ሕክምና ወይም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች ለሚሹ ሰዎች በገንዘብ መልክ የሚሰጡ የማህበረሰብ ጥቅማጥቅሞች ለማበርከት በቁርጠኝነት ይሰራል።

የዚህ ገንዘባዊ እግዛ ፖሊሲ (“FAP”) አላማ MHHS በማህበረሰቡ ውስጥ የሚያገለግላቸው ሰዎች በስርአታዊ ዘዴ መለየት እና ገንዘባዊ ድጋፍ ማድረግ ነው።

**ተግባራዊ የሚሆንባቸው ቦታዎች:**

የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው (FAP) በሁሉም በክፍል 501(c)(3) MHHS ሆስፒታሎች ስር የሚተዳደሩ ከመንግስት ፈቃድ የተሰጣቸው የሆስፒታል ተቋማት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል:

Memorial Hermann Greater Heights Hospital
Memorial Hermann Katy Hospital
Memorial Hermann Memorial City Medical Center
Memorial Hermann – Texas Medical Center
- Memorial Hermann Cypress Hospital
- Memorial Hermann Orthopedic and Spine Hospital

Memorial Hermann Northeast Hospital
Memorial Hermann Rehabilitation Hospital Katy, L.L.C.
Memorial Hermann Southeast Hospital
- Memorial Hermann Pearland Hospital

Memorial Hermann Southwest Hospital
Memorial Hermann Sugar Land Hospital
Memorial Hermann The Woodlands Medical Center
TIRR Memorial Hermann

MHHS የተመላላሽ ታካሚዎች ኢሜጂንግ ማእከላት፣ የስፖርት መድህኒት እና ማገገሚያ ማእከላት፣ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት ሆስፒታሎች ስር የሚገኙ የተመላላሽ ታካሚዎች ዲፓርትመንቶች አቅራቢዎች ላይ የተመሰረቱ የአስቸኳይ ሕክምና ማእከላት የሚያስተዳድር ሲሆን፣ እነዚህ በዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ስር ሽፋን የሚያገኙ ናቸው።

MHHS በገንዘባዊ ድጋፍ ፖሊስ ሽፋን ስር የሆኑ የተመላላሽ ታካሚዎች ዳያግኖስቲክ ላብራቶሪዎችንም ያስተዳድራል።

**<u>የፖሊሲ መግለጫ:</u>**

1. ርህራሄ እና ወካይነት የ MHHS እሴቶች እንደመሆናቸው መጠን፣ MHHS ለተቸገሩ ታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ የማድረግ ፖሊሲ ይከተላል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ታካሚዎች በ MHHS ለሚቀርብላቸው የአስቸኳይ ጊዜ ሕክምና እና ሕክማዊ ወሳኝነት ያለው ሕክምና የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኙበት አሰራር መዘርጋትም የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው አላማ ነው።

2. ለሚቀርቡላቸው አገልግሎቶች ሙሉ ክፍያ መፈጸም ለማይችሉ ግለሰዎች MHHS የገንዘብ እርዳታ እንዲያቀርብ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች እና የማመልከቻ አቀራብ ሂደትንም በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ተለይተው ቀርበዋል። አንዳንድ ሰዎች አሳማኝ ምክንያት አላቸው ተብሎ ሲታመን ያለምንም ክፍያ አገልግሎቶች ለማግኘት ብቁ እንደሚሆኑ ልብ ይበሉ (የአሰራር ክፍል 4 ይመልከቱ)።

3. ይህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ በ MHHS ሆስፒታል የሚሰጡ የአስቸኳይ ወይም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው ሕክምናዎች ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ይህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ከሆስፒታሉ ውጭ በሚገኙ የሕክምና አገልግሎቶች አቅራቢዎች እና የሐኪሞች አገልግሎቶች ላይ የጸና አይሆንም። በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ሽፋን ስር የአስቸኳይ ጊዜ እና ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው ሕክምናዎች የሚሰጡ የሆስፒታል ተቋሙ አቅራቢዎች እና ከገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ሽፋን ውጪ አገልግሎቶች የሚሰጡ አቅራቢዎች ዝርዝር ድረገጻችን ላይ ማግኘት ይችላሉ: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/. ነጻ የወረቀት ቅጂዎችም በጥያቄዎ መሰረት በሆስፒታሉ የአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት መመዝገቢያ ቦታዎች ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በ (713) 338-5502 ወይም በ 1-800-526-2121 በመደወልም ወይም በፖስታ ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

4. MHHS የገንዘብ ድጋፍ ቅናሽ በሚኖርበት ጊዜ ለማስላት የሚጠቀምበት መስፈርት MHHS ይህንን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ የ MHHS አገልግሎት ተጠቃሚ በሆነው ማህበረሰብ ውስጥ በሰፊው ለማስተዋዋቅ የሚወስዳቸው እርምጃዎች፣ የገንዘብ ድጋፍ ተጠቃሚ የመሆን ብቁነት ለመወሰን MHHS የሚከተለው ሂደት፣ እና የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ሂደት በሚመለከት የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ማብራሪያ ይዟል። MHHS ክፍያ በማይፈጸምባቸው አጋጣሚዎች የሚወስዳቸው እርምጃዎች MHHS በተባለው ሌላ ፖሊሲ ላይ ተገልጸዋል፣ የክፍያ አጠያየቅ እና የአሰባሰብ ፖሊሲ። ይህ ፖሊሲ ከ MHHS ድረገጽ ላይ ማውርድ (ዳውንሎድ ማድረግ) ይቻላል: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/፣ ወይም ነጻ የወረቀት ቅጂ የአስቸኳይ ህክምና ዲፓርትመንቱ ላይ እና የሆስፒታሉ መመዝገቢያ ቦታዎች ላይ ይገኛል። ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይም በ (713) 338-5502 ወይም በ 1-800-526- 2121 በመደወልም ማግኘት ይቻልል፣ አማራጭ 5።

5. ለገንዘባዊ ድጋፍ ብቁ ለመሆን፣ ታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ሞልተው (በአሳማኝ ግምት ብቁ ናቸው ተብሎ ለማይታመንባቸው ታካሚዎች) ከሁሉም አስፈላጊ ተጨማሪ ሰነዶች ጋር ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል። የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎች የመጀመሪያው እርስዎ የገንዘብ ድጋፍ ለጠየቁባቸው አገልግሎቶች የሚሆን የመጀመሪያ የክፍያ መግለጫ ከተላበት ቀን አንስቶ ከ 240 ቀናቶች በማይረዝም ጊዜ ውስጥ እግጁ ይሆናሉ። ልዩ ሁኔታዎች በአሰራር ክፍል 9 በተገለጸው መሰረት ሊፈቀዱ ይችላሉ። ይህ የገንዘብ ድጋፍ እና ማንኛውም በውስጡ የሚገኝ ይዘት ዛሬ በተግባር ላይ ከሚገኙትም ይሁን ለወደፊቱ ከሚወጡ የፌደራል እና የአካባቢ ሕጎች በላይ ሊሆን አይችልም።

6. ታካሚው የገንዘብ ድጋፍ ቅናሽ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ የከፈላቸው ትርፍ ክፍያዎች ካሉ፣ ሁሉም ትርፍ ክፍያ የጠከፈለባቸው የሕክምና አጋጣሚዎች ታይተው ትርፍ ክፍያው እንዲመለስለት የሚደረግ ይሆናል።

7. MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ብቁነት ለማረጋገጥ በቂ ጥረት ማድረጉን የማረጋገጥ ሙሉ ስልጣን ለ MHHS የታካሚ ስራ አገልግሎት ጽሕፈት-ቤት የተሰጠ ነው። ይህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ከርህራሄ እና ወካይነት እሴቶቹ ጋር በሚጣጣም መልኩ የ MHHS ማህበረሰብን ተጠቃሚ ለማድረግ ነው አላማው። የዚህ የገንዘብ ድጋፍ

ፖሊሲ መኖር የገንዘብ ድጋፍን ለሆነ ታካሚ የማቅረብ ግዴታን አያመለክትም ስለዚህ በውል የሚጸኑ መብቶች ወይም ግዴታዎች አይፈጥርም። ይህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ በቀጣይ ጊዜ በ MHHS ሊሻሻል እና በዳክተሮች ቦርድ ወይም እሱ በሚሰጣቸው አቅጣጫ ብቻ በሚሰሩ ተወካዮች ሊጸድቅ ይችላል።

8. እዚህ የተጠቀሱት ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ከቴክሳስ ግዛት ሕገ-ደንቦች እና ከውስጣዊ ገቢዎች ኮድ ክፍል 501(r) እና ተዛማጅ አቅጣጫዎች ጋር ተጣጥመው መሄድ ይኖርባቸዋል።

***<u>ቃላቶችና ፍቺዎቻቸው:</u>***

1. *ማመልከቻ:* በታካሚው የሚሞላ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ማለት ነው።

2. *የማመልከቻ ጊዜ:* በማመልከቻ ጊዜው፣ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ተቀብሎ ያስኬዳል። የማመልከቻ ጊዜው ሕክምናው ለግለሰቡ ከተሰጠበት ቀን ተጀምሮ ከመጀመሪያው የህክምና የክፍያ መግለጫ ቀን በኋላ በ 240ኛው ቀን የሚጠናቀቅ ይሆናል። የማመልከቻ ጊዜው ሕክምናው ለግለሰቡ በተሰጠበት ቀን ተጀምሮ ከመጀመሪያው የህክምናው የክፍያ መግለጫ ቀን በኋላ በ 240ኛው ቀን የሚጠናቀቅ ይሆናል።

3. *ጠቅላላ የሚከፈል መጠን(AGB)*: የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች ለአስቸኳይ ሕክምና ወይም ህክምናዊ ወሳኝነት ላለቸው ሕክምናዎች የሚጠየቁት የክፍያ መጠን መድህን ያላቸው ሰዎች ከሚከፍሉት አጠቃላይ ክፍያ (AGB) የማይበልጥ ይሆናል።

    a. የ MHHS የ AGB መቶኛ በ “ወደኋላ-ማየት” ዘዴ የሚሰላ ሲሆን፣ የተፈቀደው ከ Medicare ነጻ-የሆነ-የአገልግሎት ክፍያ በ 12-ወራቶች ውስጥ ለሚጠየቁ ጠቅላላ ክፍያዎች ድምር በማካፈል የሚገኝ ነው። የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ለሆኑ ታካሚዎች የሚደረጉ ቅናሾች ታካሚዎች ከ AGB የሚልቅ ክፍያ አለመጠየቃቸው ለማረጋገጥ ሲባል ከ AGB መቶኛ ገደቦች አንጻር እንዲገመገም ይደረጋል።

    b. የ AGB መቶኛዎች የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ማሳያ A -በአጠቃላይ ክፍያ የተሰሉ መጠኖች ላይ ሊገኙ ይችላሉ።

    c. የተሻሻለው የ AGB መቶኛ በየአመቱ የሚሰላ ሲሆን የበጀት አመቱ ከተጀመረ በ 120ኛው ቀን ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

4. *አመታዊ ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢ:* አንድ ቤተሰብ ከሁሉም የስራ ገቢዎች እና የጥሬ ገንዘብ ድጋፎች የሚያገኘው ግብር ያልተከፈለበት ገቢ ላይ ለህጻን ድጋፍ የሚደረግ ክፍያ በመቀነስ ለዩናይትድ ስቴትስ የውስጥ ገቢዎች አገልግሎት ሪፖርት የሚያደረገው ጠቅላላ አመታዊ ገቢ ነው። የቤተሰብ ገቢ፣ በስራ የሚገኝ ገቢ፣ የስራአጥነት ካሳ፣ የሰራተኛ ካሳ፣ የማህበራዊ ማስትና፣ የተጨማሪ ዋስትና ገቢ፣ የመንግስት እርዳታ፣ የውትድርና ተሰናባች ክፍያዎች፣ ከሞት ለተረፉ የሚደረግ ድጎማ፣ የጥሮታ ገቢ፣ ወለድ፣ የትርፍ ድርሻ፣ በፍርድቤት ትእዛዝ ለድሮ ሚስት/ባል የሚከፈል ክፍያ፣ የህጻን ድጋፍ፣ እና ከሌሎች ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን ያጠቃልላል።

5. *የተመረጡ አገልግሎቶች:* አስቸኳይ ትኩረት የማይሻ የጤና ችግር ለማከም የሚሰጡ አገልግሎቶች። የተመረጡ አገልግሎቶች ለታካሚው ጥቅም የሚሰጡ ሕክምናዎችን የሚያጠቃልሉ ሲሆኑ፣ ነገርግን አስቸኳይ ያልሆኑ እና ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው እና ሕክምናዊ ወሳኝነት የሌላቸው አገልግሎቶች፣ ማለትም መልክን ለማስተካከል ብቻ የሚደረጉ እንደ የውበት እና የጥርስ ቀዶጥገና ሕክምናዎች እንዲሁም ሌሎች በህክምና መድህን እቅዶች የማይሸፈኑ የተመረጡ ሕክምናዎችን የሚያካትቱ ናቸው። ህክምናዊ ወሳኝነት የሌላቸው የተመረጡ አገልግሎቶች ለገንዘባዊ ድጋፍ አይቀርቡም ወይም የገንዘብ ድጋፍ አይደረግላቸውም።

6. *የአስቸኳይ ሕክምና አገልግሎቶች:* ቅጽበታዊ የሕክምና ትኩረት ካልተሰጠው በስተቀር የግለሰቡን (ወይም፣ ከእርጉዝ ሴት አንጻር ደግሞ፣ ሴትየዋ ወይም ጽንሱ) ጤንነት ከባድ አደጋ ላይ የመጣል፣ ከባድ የሰውነት አካል

ጉዳት የማስከተል፣ ወይም የሆነ የሰውነት ክፍል በከፍተኛ ደረጃ የማዛባት ዕድሉ የሰፋ ነው ተብሎ የታመነበት አደገኛ የሕክምና ሁኔታ ምልክት (ከባድ ህመምን ጨምሮ) ለሚታይበት ታካሚ የሚሰጥ አገልግሎት ነው።

7. *እጅግ ልዩ የአሰባሰብ እርምጃዎች (ECAs)*: እነዚህ የሕግ ወይም የፍርድቤት ሂደትን የሚጠይቁ እንዲሁም እንደ እዳን ለሌላ አካል መሸጥ ወይም ተቃራኒ የክረዲት መረጃ ለክረዲት ኤጀንሲዎች ወይም ቢሮዎች ሪፖርት ማድረግ የመሳሰሉ እንቅስቃሴዎችን ሊያካትቱ የሚችሉ የአሰባሰብ እርምጃዎች ናቸው። MHHS ECAs ላይ እጁን አያስገባም፣ የአሰባሰብ አጋሮቹም ECAs ላይ እጃቸው እንዲያስገቡ አይፈቅድም። የ MHHS አሰባሰብ ፖሊሲዎችን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ የ MHHS ላይ ማግኘት ይቻልል፣ ሌሎች የ MHHS የክፍያ አጠያየቅ እና የአሰባሰብ ፖሊሲ፤ የዚህ ፖሊሲ ነጻ ቅጂዎች ደግሞ መስመር ላይ ይገኛሉ: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/ወይም ነጻ ቅጂዎችን በጥያቄዎ መሰረት የአስቸኳይ ህክምና ዲፓርትመንቱ እና የሆስፒታሉ መመዝገቢያ ቦታዎች ላይ አሊያም በ (713) 338-5502 ወይም በ 1-800-526-2121 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

8. *ቤተሰብ*: ታካሚው፣ የታካሚው ባለቤት/የተመሳሳይ ጋብቻ አጋር፣ የታካሚው ወላጆች ወይም ሞግዚቶች (ታካሚው ህጻን ከሆነ)፣ እና ማናቸውም በታካሚው ወይም የታካሚው ወላጆች ወይም ሞግዚቶች ቤት ላይ የሚኖሩ የታካሚው ወይም የወላጁ የገቢ ግብር ተመላሽ ላይ ተጠሪ የሆኑ ጥገኞች።

9. *የፌደራል የድህነት ወለል (“FPL”)*: አንድ ግለሰብ ዝቅተኛው የድህነት ደረጃ ላይ ነው ተብሎ እንዲፈረጅ የሚያስችል የገቢ መጠን። ይህ የገቢ ደረጃ እንደ ቤተሰብ አባላት ብዛት ይለያያል። የድህነት ወለሉ በየአመቱ በዩናይትድ ስቴትስ የጤና ዲፓርትመንት እና የሰብአዊ አገልግሎቶች እየተሻሻለ የፌደራል ሬጂስተር (መጽሔት) ላይ ይታተማል። ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ አላማ ሲባል፣ በታተሙት መመሪያዎች ላይ የተገለጸው የድህነት ወለል ያልተጣራ ገቢን የሚወክል ነው። ለዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ አላማ የሚውለው የፌደራል ድህነት ወለል በየአመቱ ይሻሻላል።

   a. የአሁኑ ጊዜ የፌደራል ድህነት ወለሎች በ ማሳያ B-የፌደራል ድህነት ወለል መመሪያዎች ገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ላይ ማግኘት ይቻላል።

10. *የገንዘብ ድጋፍ*: የገንዘብ ድጋፍ ማለት በገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ላይ የተቀመጠው የገንዘብ እና ሌላ የብቁነት መስፈርት የሚያሟሉ ታካሚዎች በ MHHS ሆስፒታሎች አማካኝነት ለሚሰጡ ህክምናዊ ወሳኝነት ላላቸው እና አስቸኳይ ሕክምና ለሚጠይቁ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች መክፈያ ይሆናቸው ዘንድ ሆስፒታል ውስጥ በ MHHS የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ነው። ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች መድህን የሌላቸው ታካሚዎች፣ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ታካሚዎች፣ እንዲሁም በከፊል የመድህን ሽፋን ያላቸው ሆነው ከቀሪ የሕክምና ክፍያዎቻቸው የተወሰነውን ወይም ሙሉውን መክፈል የማይችሉ ታካሚዎችን ያጠቃልላል።

11. *ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች*: እነዚህ አገልግሎቶች በዋናነት ለታካሚው ወይም ለሐኪሙ ምቾት ሲባል ሳይሆን አንድን የሕክምና ወይም የጤና ችግር ለመመርመር፣ በቀጥታ ለማከም፣ እና ለመንከባከብ የሚሰጡ፣ በአካባቢው የተቀመጡ የ ጥሩ ሕክምና መመዘኛዎችን የሚያሟሉ እና በ Medicare እና Medicaid ፕሮግራሞች ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው ተብለው የሚወሰዱአገልግሎቶች እና አቅርቦቶች ናቸው። ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች የውበት ቀዶጥገና ወይም እንደ ማህበራዊ፣ ትምህርታዊ ወይም የሙያ ስልጠና አገልግሎቶች የመሳሰሉ ሕክምናዊ ያልሆኑ አገልግሎቶችን አያጠቃልሉም።

12. *በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ (“PLS”)*: የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ የሚከተሉትን ያጠቃልላል: (a) የብቁነት መስፈርቶች እና የሚሰጠው ድጋፍ አጭር መግለጫ፤ (b) የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻዎች መውሰድ የሚቻልባቸው የድረገጽ እና አካላዊ መገኛዎች ዝርዝር፤ (c) ነጻ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ቅጂ እንዴት መውሰድ እንደሚቻል የሚያሳዩ መመሪያዎች፤ (5) የማመልከቻ ሂደቱ ላይ ድጋፍ የሚጠይቁበት አድራሻ የያዘ መረጃ፤ (6) የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው በሌላ ቋንቋ ተተርጉሞ የሚያገኙበት እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች፤ እንዲሁም (7) የ ገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሆኑ ታካሚዎች በአጠቃላይ ለአስቸኳይ ሕክምና ወይም ህክምናዊ ወሳኝነት ላለቸው ሕክምናዎች ከሚጠየቁት የክፍያ መጠን የበለጠ ክፍያ

እንደማይጠየቁ የሚያረጋግጥ መግለጫ።

13. *የአሳማኝ ግምት ብቁነት ወይም በአሳማኝ ግምት መሰረት ብቁ የሆነ*. አንድ መድህን የሌለው ታካሚ የገዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ መሙላት ሳያስፈልገው ታካሚው የገንዘብ ችግር እንዳለበት ያሳያል ተብሎ የሚታመነው መስፈርት አሟልቷዋል ተብሎ በሚታንበት ጊዜ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ነው።

14. *በቂ ጥረቶች*. MHHS ታካሚው ከሆስፒታል ከመውጣቱ በፊት የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን የሚመለከት በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ ለታካሚው በመስጠት ለታካሚው የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ በሚመለከት ማሳወቂያ ለመስጠት በቂ ጥረት ያደርጋል። በተጨማሪም፣ MHHS ታካሚዎችን ስለ የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ለማሳወቅ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል:

    a. *ያልተሟሉ ማመልከቻዎች*. ታካሚው እና/ወይም ቤተሰቡ ያልተሟላ ማመልከቻ ቢያስረክቡ፣ ምን ተጨማሪ መረጃ ወይም ሰነድ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ MHHS ይልክላቸዋል።

    b. *የተሟሉ ማመልከቻዎች*. ታካሚው እና/ወይም የታካሚው ቤተሰብ አባል የተሟላ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ካስገቡ ደግሞ፣ MHHS በተገቢው ጊዜ ውስጥ ታካሚው የገንዘብ ድጋፍ

    ለማግኘት ብቁ መሆኑ ወይም አለመሆኑ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ በተገቢው ጊዜ ይሰጣል እንዲሁም ይህ ውሳኔ የተወሰነባቸው ምክንያቶችን ለታካሚው (የሚቻል ከሆነ፣ ታካሚው ብቁ የሆነበት ድጋፍ በመግለጽ ጭምር) በጽሑፍ ያሳውቃል። ይህ ማሳወቂያ፣ የተፈቀደው የገንዘብ ድጋፍ መቶኛ መጠን (ተቀባይነት ላገኙ ማመልከቻዎች) ወይም ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገባቸው ምክንያት(ቶች)፣ የሚያስኬድ ከሆነ ደግሞ ከታካሚው እና/ወይም ከቤተሰቡ የሚጠበቀው ክፍያ የሚያጠቃልል ይሆናል። ታካሚው እና/ወይም ቤተሰቦቹ ሞልተው ያስረከቡት ማመልከቻ በሚገመገምበት ጊዜ መግለጫዎች ይላክላቸዋል።

    c. *የታካሚ መግለጫዎች*. MHHS የታካሚው ሂሳብ እና የሚከፈለው መጠን የሚገልጹ ተከታታይ መግለጫዎችን ይልካል። የታካሚው መግለጫዎች ታካሚው የመድህን ሽፋን ካለው ለ MHHS ማሳወቅ እንዳለበት የሚያሳስብ ጥያቄ፣ የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ማሳወቂያ፣ የገንዘብ ድጋፍ ለመጠየቅ የሚጠቀሙበት የስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ሰነዶች የሚገኙበት ድረገጽ የሚያካትቱ ናቸው።

    d. *የ MHHS ድረገጽ*. MHHS ድረገጾች የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን እና የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ሂደትን የሚገልጹ ማሳወቂያዎች በስፋት በሚታወቅ ቦታ ላይ ይለጥፋሉ። MHHS ይህንን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ሽፋን ካላቸው እና ሽፋን ከሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ጋር በቀላል ቋንቋ ከተዘጋጀ ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ፣ እና የክፍያ አጠያየቅ እና የአሰባሰብ ፖሊሲ ጋር የ MHHS ድረገጽ ላይ ይለጥፋል: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/. MHHS የእነዚህ ሰነዶች ነጻ ቅጂዎች በጥያቄዎ መሰረት እንዲያገኙ በአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት እና በመመዝገቢያ ቦታዎች ያዘጋጅላችኋል።

15. *በቂ ያልሆነ መድህን ያለው ታካሚ*: ሙሉ ወይም ከፊል የመድህን ሽፋን ያለው ሆነው ሲያበቁ ለአስቸኳይ ህክምና ወይም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያለው ህክምና የሚያወጡት ወጪ የመድህን ክፍያው ከሚሸፍነው በላይ ሲሆንባቸው ቀሪ ክፍያዉን ከኪሳቸው ለመሸፈን በቂ የገንዘብ አቅም የሌላቸው ታካሚዎች ናቸው።

16. *መድህን የሌለው ታካሚ*: ሙሉም ይሁን ከፊል የጤና መድህን ፖሊሲ ሽፋን የሌለው እንዲሁም የመንግስት ወይም

የግል የጤና መድህን፣ የጤና አበል፣ ወይም ሌላ የጤና ሽፋን ፕሮግራም (የግል መድህን፣ Medicare, ወይም Medicaid, ወይም የወንጀል ሰለባዎች ድጋፍ እና ሌሎችም ጭምር) ተጠቃሚ ያልሆነ ሰው ሆኖ ሲያበቃ፣ የደረሰበት ጉዳት በሰራተኞች ካሳ አሰራር መሰረት ሲታይ ካሳ ሊከፈለው የማይችል፣ ወይም በእዳ ወይም በሶስተኛ አካል መድህን ምክንያት ሊካስ የማይችል መሆኑን ታካሚው ራሱ ባቀረባቸው መረጃዎች ወይም በ MHHS ለሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ ሲባል ከሌሎች ምንጮች በተገኙ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ MHHS ያረጋገጠበት ታካሚ ነው።

**<u>የግምገማ መስፈርት:</u>**

1. *ተግባቦት:* ታካሚዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ማህበረሰቡ የገንዘብ ድጋፍ ስለመኖሩ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ MHHS ወደ ሆስፒታሎቹ የሚመጡ ታካሚዎችን እና ጎብኚዎችን የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን እንዲያውቁ እና ይህንን የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ በእያንዳንዱ ሆስፒታል ለሚጠቀመው ማህበረሰብ በሰፊው ለማስተዋወቅ ብዙ እርምጃዎች ይወስዳል። እነዚህ እርምጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

    a. *የታካሚ ስምምነት:* የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ለማግኘት በሚመዘገቡበት ጊዜ የሚፈረመው የጤና እንክብካቤ ስምምነት የበጎ አድራጎት አገልግሎቶች የሚያስፈልጉ ከሆነ፣ ልክ ወደ ሆስፒታል እንደገቡ ወይም ዝርዝር የክፍያ ደረሰኞች ወይ መግለጫዎች በሚያቀርቡበት ጊዜ የብቁነት ጥያቄ መቅረብ አለበት የሚል መግለጫም ያጠቃልላል።

    b. *የገንዘብ ምክር አገልግሎት:* የ MHHS ታካሚዎች የሆስፒታሉ ክፍያ ድርሻቸውን መክፈል እንደማይችሉ በሚገምቱበት ጊዜ ከሆስፒታል የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪ መረጃ እንዲጠይቁ ይበረታታሉ። የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪዎቻችን መድህን ለሌላቸው፣ በቂ መድህን ለሌላቸው፣ ወይም እኛ ለምናቀርብላቸው የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ክፍያዎች ከመክፈል ጋር በተያያዘ ሌላ የገንዘብ ተግዳረቶች ላጋጠሙዋቸው ታካሚዎች ለመርዳት የቻሉትን ሁሉ ይጥራሉ። የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪዎች ታካሚዎችን ለተለያዩ በመንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚሰሩ ፕሮግራሞች የብቁነት ማጣሪያ ሊያደርጉባቸው፣ የሰራተኛ ካሳ ወይ እዳ ጥያቄ ላይ ትብብር ሊያደርጉ፣ የክፍያ አከፋፈል እቅድ ሊያራዝሙ፣ ወይም ታካሚዎች የገንዘብ ድጋፍ እንዲጠይቁ ሊተባበሩዋቸው ይችላሉ።

    c. *በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ እና ማመልከቻ:* የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው በቀላል ቋንቋ የቀረበ ጥቅል መረጃ የወረቀት ቅጂ እና የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻው የወረቀት ቅጂ ሁሉም ታካሚዎች አገልግሎት በሚያገኙበት ጊዜ ቶሎ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። MHHS የእነዚህ ሰነዶች ነጻ ቅጂዎች በጥያቄዎ መሰረት እንዲያገኙ በ አስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት እና በመመዝገቢያ ቦታዎች ያዘጋጅላቹዋል። ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይም በ 713-338-5502 ወይም በ 1-800-526-2121 በመደወልም ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

    d. *የተተረጎሙ ቅጂዎችም አሉ:* MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው፣ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀው ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻው፣ እና የክፍያ አጠያየቅ እና አሰባሰብ ፖሊሲ የኢንግሊዝኛ ብቃት ውስኑነት ላላቸው ከ አምስት በመቶ (5%) የሚያንሱ ወይም ለ 1,000 የሆስፒታሎቹ ተገልጋይ የማህበረሰቡ አባላት ተርጉሞ ይሰጣል። MHHS የእነዚህ ሰነዶች ነጻ ቅጂዎችን የMHHS ድረገጽ ላይ እንዲሁም ከአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንቱ እና ከሆስፒታል መመዝገቢያዎ ቦታዎች ላይ ጠይቀው ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል። በተጨማሪም ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይም በ713-338-5502 ወይም በ 1-800-526-2121 በመደወልም ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

    e. *አመልካች ማሳወቂያ.* ሁሉም የገንዘብ ድጋፍ አመልካች ማሳወቂያዎች በ MHHS የአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት እና የታካሚዎች መመዝገቢያ ቦታዎችን ጨምሮ ለህዝቡ በግልጽ በሚታዩ ቦታዎች በግልጽ እና በጉልህ፣ እንደሚታዩ ሆነው

ይለጣፋሉ። አመልካች ማሳወቂያው የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን እና ተጨማሪ መረጃ ለመጠየቅ የሚያስችሉ የእያንዳንዱን የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪ ስልክቁጥር ያሳያሉ።

f. *ድረገጽ*: የ MHHS ድረገጾች የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን የሚገልጽ ማሳወቂያ ከገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻው አሰራር ማብራሪያ ጋር በማድረግ ብዙ ሰው በሚያውቀው ቦታ ይለጥፋሉ። MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን ሽፋን ካላቸው እና ሽፋን ከሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ጋር፣ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀው ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ፣ እና የክፍያ አጠያየቅ እና የአሰባሰብ ፖሊሲ የ MHHS ድረገጽ ላይ ይለጥፋል: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/

g. *የታካሚ ክፍያ መጠየቂያዎች እና መግለጫዎች*: የታካሚ መግለጫዎች ታካሚው ማንኛውም አይነት የጤና መድህን ካለው ለ MHHS የማሳወቅ ሃላፊነት እዳለበት የሚገልጽ ጥያቄ የሚያካትቱ ሲሆን፤ የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ማሳወቂያ፣ የገንዘብ ድጋፍ የሚጠይቁበት የስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ሰነዶች የሚገኙበት የድረገጽ አድራሻ ጭምር ያጠቃልላሉ።

h. *ፖስታ ወይም ፋክስ*: ታካሚዎች የእነዚህን ሰነዶች ነጻ ቅጂዎች ለማግኘት ሙሉ ስማቸውን እና MHHS ቅጂዎቹን እንዲልክላቸው የፖስታ ምላሽ መላኪያ አድራሻቸውን በማካተት ከታች ወዳለው አድራሻ የጽሑፍ ጥያቄያቸውን በፖስታ ወይም በፋክስ መላክ ይችላሉ።

Memorial Hermann Health System
Attn: Financial Assistance
909 Frostwood
Suite 3:100
Houston, Texas 77024
ፋክስ: 713-338-6500

2. *ብቁነትን መወሰን*: የገንዘብ ድጋፍ ውሳኔ የሚተላለፈው የግለሰቡ የገንዘብ ፍላጎት ግምገማ አሰራርን በመከተል ነው። እነዚህ አሰራሮች ከታች ተገልጸዋል:

a. በአሳማኝ ግምት ላይ የተመሰረተ የብቁነት ውሳኔ የሚወሰነው ከታች በ ክፍል 4 በተቀመጠው መስፈር መሰረት ነው። አንድ ታካሚ በአሳማኝ ግምት መሰረት ለገንዘብ ድጋፍ ብቁ ሆኖ ከተገኘ፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ መሙላት አይጠበቅበትም። ይሁን እንጂ፣ ታካሚው ወይም እርዳታ ሰጪው በማጣራት ሂደቱ የመተባበር እንዲሁም የአሳማኝ ግምት ብቁነት ለመወሰን የሚያስፈልጉ የግል ወይም ገንዘባዊ መረጃ እና ሰነድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤

b. ታካሚው ወይም እርዳታ ሰጪው በማጣራት ሂደቱ የመተባበር እንዲሁም የአሳማኝ ግምት ብቁነት ለመወሰን የሚያስፈልጉ የግል ወይም ገንዘባዊ መረጃ እና ሰነድ እንዲያቀርቡ የሚጠበቁበት የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ሂደት፤

c. MHHS የአንድን ግለሰብ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ-ብቁነት ለመወሰን በቂ ጥረት ካደረገ በኋላ ግለሰቡ ከሆስፒታል ከመውጣቱ በፊት የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲን የሚያብራራ በቀላል ቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ የያዘ ማሳወቂያ ለታካሚው ለመስጠት ጭምር በቂ ጥረት ያደርጋል። በተጨማሪም፣ MHHS ታካሚዎችን ስለ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ለማሳወቅ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል:

i. *ያልተሟሉ ማመልከቻዎች*: ታካሚው እና/ወይም ቤተሰቡ ያልተሟላ ማመልከቻ ቢያስረክቡ፣ MHHS የመጀመሪያው ማመልከቻ በተቀበለ በአርባ አምስት (45) ቀናቶች ውስጥ ምን

ተጨማሪ መረጃ ወይም ሰነድ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ የጽሑፍ ማሳወቂያ ይልከላቸዋል።

ii. *የታካሚ መግለጫዎች:* የታካሚው መግለጫዎች ታካሚው የመድህን ሽፋን ካለው ለ MHHS የማሳወቅ ሀላፊነት እንዳለበት የሚገልጽ ይዘት፣ የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ማሳወቂያ፣ የገንዘብ ድጋፍ ለመጠየቅ የሚጠቀሙበት የስልክ ቁጥር፣ እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ሰነዶች የሚገኙበት ድረገጽ የሚያካትቱ ናቸው።

iii. *የMHHS ድረገጽ:* የ MHHS ድረገጾች የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን እና የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ሂደትን የሚገልጹ ማሳወቂያዎች በስፋት በሚታወቅ ቦታ ላይ ይለጥፋሉ። የ MHHS ድረገጽ: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/, MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲውን ሽፋን ካላቸው እና ሽፋን ከሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ጋር፣ ከቀላል ቋንቋ ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ፣ እና የክፍያ አጠያየቅ እና አሰባሰብ ፖሊሲይለጥፋል።

iv. *ሰነዶች ጠይቆ መውሰድ ይቻላል:* MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን ሽፋን ካላቸው እና ሽፋን ከሌላቸው አቅራቢዎች ዝርዝር ጋር፣ ከቀላል ቋንቋ ጥቅል መረጃ፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ፣ እና የክፍያ አጠያየቅ እና አሰባሰብ ፖሊሲ ይለጥፋል በጥያቄ መሰረት መውሰድ እንዲቻል የአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንት እና የመመዝገቢያ ቦታዎች ላይ እንደሚገኙ ያደርጋል።

d. በ TransUnion ወይም Experian የመበደር አቅምዎ ጨምሮ የታካሚው ወይም የእርዳታ ሰጪው የመክፈል ብቃት የሚሳዩ ይፋ የሆኑ ውጫዊ ዳታዎችን መጠቀም፤

e. ቀደም ሲል በ MHHS ለተሰጡ አገልግሎቶች መክፈያ ሊሆኑ የሚችሉ የታካሚው ያልተከፈሉ ሒሳቦችን እንዲሁም የታካሚው ክፍያዎች እና ሊመለሱ የማይችሉ ወይም የባከኑ ብድሮችን መገምገም፤

f. በ MHHS የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ደረጃዎች የገቢ፣ የቤተሰበ አባላት ብዛት፣ እና የፌደራል ድህነት ወለል ላይ የተመሰረተ ነው። መድህን ያላቸው እና የሌላቸው ታካሚዎች ሁለቱም የገንዘብ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ፤ እንዲሁም

g. የአንድን ታካሚ የገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ከታች ያለው መስፈርት ላይ የተመሰረተ ሲሆን እንደ ታካሚው የገንዘብ አቅም ሁኔታ፣ እየቀነሰ የሚሄድ የገንዘብ አቅም ሁኔታ፣ እንዲሁም የሶስተኛ አካል የጤና ጥቅማጥቅሞች ከመኖር ጋር በተያያዘ የተለያየ

ሊሆን ይችላል። የብቁነት መመሪያዎች በየአመቱ የፌደራል ድህነት ወለል መመሪያዎች በፌደራል መንግስት ከታተሙ በኋላ ይሻሻላሉ። ከታች ከተጠቀሱት መመሪያዎች የሚልቅ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ለ ክፍያ እቅድ ከግምት እንዲገቡ የማጣራት ስራ ሊሰራባቸው ይችላል።

3. *የታካሚ ገንዘባዊ ድጋፍ ብቁነት:* በፌደራል ድህነት ወለሎች መሰረት፣ የሚከተለው መስፈርት ለገንዘባዊ ድጋፍ ብቁ ለሆኑ መድህን የሌላቸው እና በቂ መድህን የሌላቸው ታካሚዎች የሚደረግ ቅናሽ ለመወሰን ጥቅም ላይ መዋል ይኖርበታል። በቂ መድህን የሌላቸው ታካሚዎች ለበጎ አድራጎት ብቁ ከመሆናቸው በፊት መድህናቸውን ማስከፈል ይጠበቅባቸዋል። ለገንዘባዊ ድጋፍ ብቁ ለሆኑ ታካሚዎች የሚደረጉ ቅናሾች ታካሚዎቹ ከ AGB በላይ ክፍያ አለመጠየቃቸውን ለማረጋገጥ ከ AGB መቶኛ ገደብ አንጻር ይገመገማሉ።

a. **ነጻ ሕክምና**:

i. መድህን የሌለው ታካሚ አመታዊ ያልተጣራ የቤተሰብ ገቢ ያልተጣራ ገቢ ገንዘባዊ ድጋፍ ብቁነት ሰንጠረዥ ላይ እንደተገለጸው፣ ከአሁን የፌደራል የድህነት መመሪያዎች አንጻር በመቶኛ ሲሰላ ሁለት መቶ (200%) ወይም ያነሰ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ፣(ማሳያ A -በአጠቃላይ ክፍያ የተሰሉ መጠኖች)፣ ታካሚው (ሌላ ሀላፊነት የሚወስድ አካል) ነጻ ሕክምና (100% ቅናሽ)

የማግኘት መብት ስለሚሰጠው ምንም ያልተከፈለ ቀሪ ሒሳብ አይኖሮውም።

ii. በ Medicare አማካኝነት አንደኛ ደረጃ የጤና ሽፋን የሚያገኙ ሆነው ሲያበቁ በ Medicaid አማካኝነት ደግሞ ለሁለተኛ ሽፋን ብቁ የሆኑ ታካሚዎች የ Medicaid ክፍያ ከተከፈለልዎ እና ከ THMP ወይም ከ Managed Medicaid ከፋይ የሚጠይቁት ክፍያ ተወስኖልዎ ከተቀበሉ በኋላ ለሚቀረው ያልተከፈለ ሒሳብ መጠን መቶ ፐርሰንት (100%) ቅናሽ ብቻ ይደረግልዎታል።

b. **ቅናሽ የተደረገበት ሕክምና:**

i. ከአሁኑ የፌደራል የድህነት መመሪያዎች አንጻር ሲታይ ከሁለት መቶ ፐርሰንት (200%) የሚልቅ ከአራት መቶ ፐርሰትንት (400%) ግን የማይበልጥ ያልተጣራ አመታዊ የቤተሰብ ገቢ ያላቸው ታካሚዎች/ግለሰቦች መድህን ያላቸው ታካሚዎች ከሚከፍሉት ጠቅላላ የክፍያ መጠን (AGB) የሚስተካከል ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

ii. የሆስፒታል ክፍያ መጠየቂያዎች ላይ ገና ያልተከፈለ ሒሳብ ያላቸው ታካሚዎች፣ የሚከተሉት መስፈርቶች በሙሉ የሚያሟሉ ከሆነ ቅናሽ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ: 1) የሒሳብ መጠኑ ከግለሰቡ አመታዊ ያልተጣራ የቤተሰብ ገቢ አስር በመቶ (10%) የሚበልጥ ከሆነ፤ 2) ቀሪ ክፍያውን በሙሉ ወይም በከፊል መክፈል የማይችሉ ከሆነ፤ እንዲሁም 3) ያልተከፈለው የሒሳብ መጠን ቢያንስ $5,000 ሲሆን። በእነዚህ አጋጣሚዎች ጊዜ፣ ታካሚው ወይም ተያዡ ከገንዘባዊ ድጋፍ ፖሊሲው ሂደት ጋር መተባበር እና የብቁነት ውሳኔ ለመወሰን የሚያስፈልጉ የግል መረጃዎች እና ሰነዶች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ታካሚው ተቀባይነት ካገኘ ያልተከፈለው ቀሪ ሂሳብ ለመሸፈን ከአመታዊ ያልተጣራ የቤተሰብ ገቢያቸው ከአስር በመቶ (10%) የማይበልጥ መጠን እንዲከፍሉ ይደረጋል ወይም ከታካሚው የገንዘብ አቅም ሁኔታ አንጻር የበለጠ ታካሚውን ይጠቅመዋል ተብሎ ከታመነ የ AGB ቅናሽ ተግባራዊ ይደረጋል።

4. *አሳማኝ ግምት ላይ የተመሰረተ ብቁነት:* መድህን የሌላቸው ታካሚዎች ከታች ከተዘረዘሩት መስፈርቶች ውስጥ አንዱን የሚያሟሉ ሆነው ከተገኙ ብቁ ሊሆኑ የሚችሉበት እድል አለ። ቢያንስ ከመስፈርቶቹ አንዱ ከተረጋገጠ በኋላ የገቢ ማረጋገጫ መጠየቅ አያስፈልግም። ከታች የቀረቡት ሁኔታዎች፣ የታካሚው የቤተሰብ ገቢ ከፌደራል ድህነት ወለል በሁለት እጥፍ ያነሰ የሚሆንበት እና ታካሚው መቶ በመቶ (100%) የሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው ሕክምናዎች ክፍያዎች ቅናሽ ብቁ የሚሆንበት አጋጣሚ የሚያሳይ ነው። መድህን በሌለው ታካሚ ላይ የሚደረግ የአሳማኝ ግምት ብቁነት ማጣሪያ ልክ ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች ከተሰጡት በኋላ የአገልግሎቶቹ ክፍያ መጠየቂያ ከመዘጋጀቱ በፊት በፍጥነት መከናወን አለበት። MHHS አንድ ታካሚ የአሳማኝ ግምት ብቁነት የማግኘት መስፈርት ሊያሟላ ይችላል የሚል ማሳወቂያ ከደረሰው፣ የአሳማኝ ግምት ብቁነት ግምገማ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሁሉንም የታካሚው መግለጫዎች ለሰላሳ (30) ቀናቶች እንዲራዘሙ ያደርጋል። የሶስተኛ አካል መድህን (እንደ Medicaid ከመሳሰሉት የግዛት ወይም የአካባቢው የድጋፍ ፕሮግራሞች ውጪ) ያላቸው ታካሚዎች ለአሳማኝ ግምት ብቁነት ከግምት አይገቡም እንዲሁም የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ማስረከብ ይጠበቅባቸዋል።

a. የሚከተሉት መስፈርቶች የሚያሟሉ መድህን የሌላቸው ታካሚዎች የአስቸኳይ ሕክምና እና ሕክምናዊ ወሳኝነት ያለው ሕክምና መቶ በመቶ(100%) ቅናሽ ማግኘት ለሚያስችላቸው የአሳማኝ ግምት ብቁነት ከግምት ይገባሉ:

i. ቤትአልባ ወይም ከቤትአልባ ክሊኒክ የሕክምና እንክብካቤ የተሰጠው፤
ii. የሴቶች፣ ጨቅላዎች እና ህጻናት ፕሮግራሞች (WIC) ላይ መሳተፍ፤
iii. የምግብ እርዳታ ብቁነት፤
iv. የማሟያ ኒዩትሪሽን ድጋፍ ፕሮግራም (SNAP)፤

v. የሌሎች የግዛት ወይም የአካባቢ የድጋፍ ፕሮግራሞች ብቁነት (ለምሳሌ፣ Medicaid ትርፍ-ገቢ)፤
vi. የዝቅተኛ ገቢ/የድጎማ መኖሪያ ቤት እንደ ቅቡል አድራሻ ቀርቧል፤
vii. ለሕክምናዊ አገልግሎቶች የተሰጡ እርዳታዎች ደረሰኝ፤
viii. የአእምሮ ድክመት አለ፣ነገር ግን በታካሚው ፈንታ ነገሮችን ማስኬድ የሚችል ማንም የለም፤
ix. የቅርብ ጊዜ የግለሰቡ ኪሳራ፤
x. በቅጣት ወህኒቤት መታሰር፤
xi. ታካሚው ምንም የሚታወቅ ንብረት ወደማይገኝለት ደረጃ ወርዷል ፤ ወይም
xii. በኤሌክትሮኒክ ነጥብ መስጫ ሞዴል (ከታች የተገለጸው) በተወሰነው መሰረት።

b. **ኤሌክትሮኒክ ነጥብ መስጫ ሞዴል:** መድህን የሌለው ታካሚ ወይም ተያዥ የገንዘብ ክፍያ ፖሊሲ ማመልከቻ ሳይሞላ ከቀረ ወይም ብቁነት ለመወሰን የሚያስፈልጉ ገንዘባዊ ሰነዶች ካላቀረበ፣ ገንዘባዊ ደረጃ፣ የከዚህ ቀደም በጎ አድራጎት ሁኔታ፣ የስራ ሁኔታ፣ ዚፕ ኮድ፣ ዕድሜ፣ የክፍያ ታሪክ፣ የከዚህ ቀደም የባከነ ዕዳ፣ እና ወደ ሕክምናው የተላከበት ምንጭ በሚያካትት መስፈርት መሰረት ውጤቶችን የሚሰጥ ኤሌክትሮኒክ ነጥብ መስጫ ሞዴል (ESM) በመጠቀም ሒሳቡ እንዲጣራ ይደረጋል። የ ESM ውጤቱ ሂሳቡ ለገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲው ብቁ የመሆን እድሉ ከፍተኛ መሆኑ የሚያመላክት ከሆነ፣ መድህን አልባ የሆነው ሂሳብ ይህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ በሚፈቅደው መሰረት በአሳማኝ ግምት ላይ የተመሰረተ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ቅናሽ የሚደረግለት ይሆናል።

5. *የቡቅነት የጊዜ ሰሌዳ:*

a. መድህን ለሌላቸው ታካሚዎች፣ የገንዘብ ድጋፍ እና የአሳማኝ ግምት ብቁነት ውሳኔ ለሁሉም በታካሚው ሊከፈሉ ክፍት የነበሩ የሒሳብ መጠኖች ወደኋላ ጭምር ተመልሶ እንዲሁም አሁን እየተሰጡ የሚገኙት ሕክምናዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። የታካሚዎች ብቁነት በአሰራር ክፍል 3 ላይ በተቀመጡት ወሳኝ ምክንያቶች መሰረት የሚወሰን ሲሆን ፈጣን ወይም ያልዘገዩ ክፍያዎች አድርገው በመቆየታቸው ማግኘት የነበረባቸውን ጥቅም አያሳጣቸውም። በተጨማሪም፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ የሞላ ታካሚ ደግሞ ታካሚው ምንም ተጨማሪ እርምጃ መውሰድ ሳያስፈልገው ለስድስ ወራት ያህል ወደ ኋላ ተመልሶ የሚሰራ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ያገኛል። ማናቸውም ባለፉት ስድስት (6) ወራቶች ውስጥ በታካሚው የገንዘብ አቅም ሁኔታ ላይ የተፈጠሩ በገንዘብ ድጋፍ ብቁነት ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ተጨባጭ ለውጦች በሚኖሩበት ጊዜ ታካሚው ለውጡ በተከሰተ በሰላሳ (30) ቀናቶች ውስጥ ለ MHHS ማሳወቅ ይኖርበታል። ታካሚው በቤተሰብ ገቢያቸው ላይ የተከሰተው ተጨባጭ ለውጥ ሳያሳውቁ ቢቀሩ MHHS ይሰጣቸው የነበረው ማንኛውም የገንዘብ ድጋፍ ለውጡ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ እንዲያቋርጥ ሊገደድ ይችላል።

6. *አስቸኳይ ሕክምና ወይም ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች:* የገንዘብ ድጋፍው ሆስፒታል ውስጥ ለሚሰጡ የአስቸኳይ ሕክምናዎች ወይም ሕክምናዊ ወሳኝነት ላለቸው አገልግሎቶች ብቻ የሚሰጥ ነው። በዚህ ክፍል የተካተቱት ይዘቶች በ ፌደራል ወይም ግዛት ሕግ ላይ ተመስርቶ የታካሚው የመክፈል አቅም ምንም ይሁን ምን ከግምት ሳይገባ በሚሰጠው የአስቸኳይ ሕክምና እና ሕክምናዊ ወሳኝነት ያላቸው አገልግሎቶች ከማቅረብ አንጻር የ MHHS ግዴታ ወይም አሰራሮች ላይ ለውጥ ለማድረግ የታሰቡ አይደሉም።

7. *የማመልከቻ ሂደት*

a. *እንዴት ማመልከት ይችላሉ:* የገነዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ ሞልቶ ከተጨማሪ ማጠናከሪያ ሰነዶች ጋር ማስረከብ የግድ ይላል። ነጻ የማመልከቻው ቅጂዎች ከ MHHS ድረገጽ ላይ ማውረድ ይቻላል: http://www.memorialhermann.org/financialassistanceprogram/. ነጻ የወረቀት ቅጂዎቹን የአስቸኳይ ሕክምና ዲፓርትመንቱ ላይ እና የሆስፒታሉ መመዝገብያ ቦታዎች ላይ ማግኘት ይቻላል። ነጻ የወረቀት ቅጂዎችን በፖስታ ወይም በ 713-338-5502 ወይም በ 1-800-526-

2121 በመወደወልም ማግኘት ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

b. አመልካቾች የሞሉዋቸው ማመልከቻዎችን እና ተጨማሪ ማጠናከሪያ ሰነዶችን ወደ ሆስፒታሉ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪ መላክ ወይም ከታች ወደ ተጠቀሰው አድራሻ በፖስታ መላክ ይችላሉ። ታካሚዎች ወደ መረጃ ዴስክ ሄደው ከገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪ ጋር መነጋገር እንደሚፈልጉ በመግለጽ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪውን ማግኘት ይችላሉ። የማመልከቻው አሞላል በተመለከተ ጥያቄዎች ለማቅረብ፣ ማመልከቻው በመሙላት ሂደት ድጋፍ ስለመጠየቅ፣ ወይም ያስረከቡት ማመልከቻ በምን ሁኔታ እንደሚገኝ ለማወቅ፣ በአካል ሆስፒታል ድረስ በመሄድ የሆስፒታሎቹ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪዎችን ማናገር ይችላሉ ወይም በ 713-338-5502 ወይም በ 1-800-526-2121 መደወል ይችላሉ፣ አማራጭ 5።

c. የተሞሉ ማመልከቻዎችን ወዴት መላክ ይችላሉ:

Memorial Hermann Health System
Attn: Financial Assistance
909 Frostwood
Suite 3:100
Houston, Texas 77024

-ወይም-

ፋክስ: 713-338-6500

d. ለገንዘብ ድጋፍ ወይም የአሳማኝ ግምት ብቁነት ከግምት የመግባት ጥያቄዎች በማመልከቻ ጊዜው ውስጥ በሚከተሉት ግለሰቦች ሊቀርቡ ይችላሉ: (i) ታካሚው ወይም ተያዡ፤ (ii) የታካሚው ወይም የተያዡ ተወካይ፤ (iii) የ MHHS ተወካይ በ ታካሚው/አመልካቹ ፋንታ፤ ወይም (iv) ታካሚውን የሚከታተል ሐኪም።

e. በዚህ የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ሌላ ቦታ ላይ የተገለጹ ከግምት የመግባት ሁኔታዎች እንዳሉ ሆነው፣ ታካሚው ከገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ሂደቱ ጋር የመተባበር ሙሉ ተሳትፎ የማድረግ ሀላፊነት አለበት። ይህ የሶስተኛ አካል የጤና ሽፋን የሚመለከት መረጃ ማቅረብ፤ ሁሉም በመንግስት ወይም በሌላ ፕሮግራሞች (ለምሳሌ፣ Medicare, Medicaid, ሶስተኛ አካል ሀላፊነት የሚወስድበት ክፍያ፣ የወንጀል ሰለባዎች ገንዘባዊ እርዳታ፣ ወዘተ) አማካኝነት የገንዘብ ድጋፍ የማግኘት ጥያቄ ለማቅረብ ወይም የታካሚው ለሌላ የገንዘብ ድጋፍ ብቁ መሆን ለመወሰን የሚያስፈልጉ ሰነዶች እና ማረጋገጫዎች በጊዜው እና ወድያውኑ ማቅረብን ያጠቃልላል። እነዚህን ማድረግ አለመቻል የታካው ለገንዘብ ድጋፍ ብቁነት የመታየት እድል ላይ አሉታዊ ጫና ሊያሳድር ይችላል። ታካሚዎቹ MHHS ጥያቄ ካቀረበበት ጊዜ አንስቶ መረጃው፣ ማረጋገጫዎቹ እና ሰነዶቹን በሰላሳ (30) ቀናቶች ውስጥ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፣ አለያም ደግሞ ይህ ሳያደርጉ የቀሩበት አሳማኝ ምክንያት ለ MHHS ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ከአሳማኝ ግምት ብቁነት በስተቀር፣ የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ የግድ በታካሚው (ወይም ተያዡ/ ተወካዩ) ነው መሞላት እና መፈረም ያለበት።

f. የገንዘብ ድጋፍ መጠየቂያ ማመልከቻ በሚሞሉበት ጊዜ የገንዘብ ምክር አገልግሎት ሰጪው ሊተባበረዎት ይችላል። ታካሚው ከሞተ እና በእሱ ፋንታ ሀላፊነት ሊወስድ የሚችል አካል ለይቶ ማወቅ ካልተቻለ፣ የ MHHS ተወካይ ጥያቄውን ሊያመነጭ እና የተገኙት መረጃዎች እና ሰነዶች ተጠቅሞ ማመልከቻውን ሊሞላ ይችላል።

8. *የቤተሰብ ገቢ:*

a. ታካሚው የቤተሰብ ገቢ ለመመስረት ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ (ሰነዶቹ የሚገኙ ከሆነ) አንድ ወይም ከአንድ በላይ ማቅረብ ይችላል። የታካሚው ቤተሰብ አባላቶች ውስጥ ከአንድ በላይ ስራ የተቀጠረ ሰው ካለ፣ እያንዳንዱ ሰው የግድ ከሚከተሉት ሰነዶች ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ማቅረብ ይኖርበታል:

   i. በቅርብ ጊዜ የተሞላ የፌደራል ገቢ ግብር ቅጽ፤
   ii. የግርብ ጊዜ W-2 እና 1099 ቅጾች፤
   iii. የክርብ ጊዜ የክፍያ ደረሰኝ (ወይም፣ የሚያስኬድ ከሆነ፣ የስራአጥነት መግለጫ ቅጂ፣ የማህበራዊ ዋስትና ደብዳቤ፣ ወዘተ)፤
   iv. የጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተፈጸመበት የአሰሪ የክፍያ መግለጫ፤ ወይም
   v. ማንኛውም የቤተሰቡ ገቢ በተመለከተ ከሶስተኛ አካል የተገኘ ማረጋገጫ።

b. ታካሚው ቢያንስ ከላይ ከተጠቀሱት ሰነዶች ውስጥ አንድ የእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል (ታካሚውን ጨምሮ) ገቢ የሚያንጸባርቅ ሰነድ ማቅረብ ከቻለ እና ማረጋገጫው ላይ ፊርማውን ካኖረ፣ ታካሚው ሰነዶቹን ማቅረብ በማይችልበት ሁኔታ ደግሞ ማረጋገጫው ላይ ፊርማው ያኖረ ሰው ይህ ማድረግ ከቻለ፣ ሙሉ ሰነዶች አልቀረቡም ተብሎ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻው ያልተሟላ ሊባል አይችልም።

c. ከአሳማኝ ግምት ብቁነት በስተቀር፣ አመልካቹ የግድ የማመልከቻ ማረጋገጫው ላይ መፈረም መቻል አለበት። MHHS በኋላ ላይ አመልካቹ በተጨባጭ የውሸት መረጃ ማቅረቡን የሚያሳይ ማስረጃ ካገኘ ውሳኔውን ሊሰርዝ ወይም ሊያሻሽል ይችላል።

*ተጨማሪ ሰነዶች*: የ MHHS የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ የንብረት ወይም ወጪዎች ሰነዶች አይጠይቅም። ይሁን እንጂ አመልካቾች የገንዘብ ችግራቸውን በማሳየት ይህንን ችግራቸው ሳያሳዩ ሊያገኙት ይችሉ ከነበረው የገንዘብ ድጋፍ ፖሊሲ ብቁነት እኩል ወይም የበለጠ የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ሊረዱዋቸው ይችላሉ ብለው ያመኑባቸው ንብረቶች፣ ወጪዎች፣ ገቢ፣ ያልተከፈለ እዳ፣ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ተጨማሪ ሰነዶችን ለማቅረብ ሊወስኑ ይችላሉ።

9. *የውሸት ወይም አሳሳች መረጃ*: አመልካቾች የሕክምና ወጪዎች የመሸፈን አቅማቸው በሚመለከት ሆን ብለው የውሸት ወይም አሳሳች መረጃ ማቅረባቸው ከተረጋገጠ፣ MHHS የአመልካቹን የአሁን ወይም የቀጣይ ጊዜ ማመልከቻዎች ውድቅ ሊያደርግ ይችላል። ሆን ተብሎ ሳይሆን በስህተት የቀረበ የሀሰት መረጃ በሚኖርበት ጊዜ ደግሞ፣ MHHS እውነተኛው መረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔውን ይሰጣል። አመልካቹ ሆን ብሎ ባቀረበው የውሸት መረጃ መሰረት የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት የጀመረ ከሆነ ደግሞ፣ MHHS ታካሚው ከዚህ ቀደም የወሰደውን የገንዘብ ድጋፍ ይሰርዛል፣ እንዲሁም MHHS ሕጋዊ መብቶቹን በመጠቀም ታካሚው ቀደም ሲል የወሰዳቸው ክፍያዎችን እንዲመልስ ሊያደርግ ይችላል። የሀሰት መረጃው ሆን ተብሎ ሳይሆን ባለማወቅ የቀረበ ከሆነ ደግሞ፣ MHHS እውነተኛው መረጃ ላይ ተመስርቶ ውሳኔውን ያሻሽላል።

**ማጣቀሻዎች:**

የታካሚ ዝውውር ፖሊሲ (EMTALA እና የቴክሳስ ዝውውር ድንጋጌ ማክበር) የገንዘብ ድጋፍ
እቅድ በተመለከተ በቋንቋ የተዘጋጀ ጥቅል መረጃ
የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ
የክፍያ አጠያየቅ እና አሰባሰብ ፖሊሲ

**<u>ማሳያዎች:</u>**

ማሳያ A-በአጠቃላይ ክፍያ የተሰሉ መጠኖች

ማሳያ B-የፌደራል ድህነት መመሪያዎች

*በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል።*

## ማሳያ A-በአጠቃላይ ክፍያ የተሰሉ መጠኖች

ጠቅላላ የሚከፈል መጠን MHHS በ Medicare አማካኝነት ለአስቸኳይ ወይንም ሕክምናዊ ወሳኝነት አገልግሎቶች ለሚከፈል ክፍያ በሚጠቀምበት የክፍያ አጠያየቅ እና የኮዲንግ አሰራር መሰረት የሚሰላ ይሆናል።

ከ Medicare የተፈቀደ ጠቅላላ ክፍያ ለነዚያ የክፍያ ጥያቄዎች ለተከፈለው ጠቅላላ ክፍያ በማካፈል የተገኘው ውጤት ከ ၊ በመቀነስ የ AGB መቶኛ ማስላት ይቻላል።

**AGB % ለ IP (ተኝቶ ታካሚ) = Medicare IP የተፈቀደ ክፍያ / Medicare IP ጠቅላላ ክፍያዎች**
**AGB % ለ OP (ተመላላሽ ታካሚ) = Medicare OP የተፈቀዱ ክፍያዎች / Medicare OP ጠቅላላ ክፍያዎች**

በየአመቱ AGB ለእያንዳንዱ ሆስፒታል ለየብቻ ነው የሚሰላው፣ ነገርግን ሁሉም የ MHHS ሆስፒታሎች ከሁሉም ሆስፒታሎች መካከል ያነሰውን AGB ይቀበላሉ።

| ተቋማት | ተኝቶ ታካሚ | ተመላላሽ ታካሚ |
|---|---|---|
| Memorial Hermann Greater Heights Hospital | 27% | 11% |
| Memorial Hermann – Texas Medical Center | 20% | 11% |
| Memorial Hermann Katy Hospital | 27% | 10% |
| Memorial Hermann Rehabilitation Hospital – Katy | 39% | 11% |
| Memorial Hermann Memorial City Medical Center | 26% | 13% |
| Memorial Hermann Northeast Hospital | 27% | 11% |
| Memorial Hermann Southeast Hospital | 27% | 11% |
| Memorial Hermann Southwest Hospital | 24% | 14% |
| Memorial Hermann Sugar Land Hospital | 25% | 11% |
| Memorial Hermann The Woodlands Medical Center | 26% | 12% |
| TIRR Memorial Hermann | 29% | 17% |
| University Place | 50% | N/A |

የ 2022 በጀት አመት (ሐምሌ 2021 – ሰኔ 2022) AGB መጠኖች የሚከተሉት ናቸው:

**ጠቅላላ የሚከፈል መጠን OP: 10%**
**ጠቅላላ የሚከፈል መጠን IP: 20%**

*በሚቀጥለው ገጽ ይቀጥላል።*

**<u>ማሳያ B-የፌደራል ድህነት መመሪያዎች</u>**

ያልተጣራ ወርሀዊ ገቢ የገንዘብ እገዛ ብቁነት ሰንጠረዥ የፌደራል ድህነት መመሪያዎች ላይ ለውጦች በሚደረጉበት ጊዜ ነው የሚሻሻለው። ሰንጠረዡ በየአመቱ ይሻሻላል።

ያልተጣራ ወርሀዊ ገቢ የገንዘብ እገዛ ብቁነት ሰንጠረዥ ማለት MHHS በዚህ FAP ስር ይህንን የገንዘብ እገዛ ብቁነት ለመሰን የሚጠቀምበት የአሁኑ የገቢ ሰንጠረዥ ነው።

ያልተጣራ ወርሀዊ ገቢ የገንዘብ እገዛ ብቁነት ሰንጠረዥ የፌደራል ድህነት መመሪያ የሃሪስ ካውንቲ ሆስፒታል ዲስትሪክት ብቁነት ሰንጠረዥ ላይ የጠመሰረተ ሲሆን፣ ይህ በእነዚህ የመንግስት አካላት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚሻሻል ነው፣

እባክዎ ከታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ:

| **Memorial Hermann Health System**<br>ያልተጣራ ወርሀዊ ገቢ የገንዘብ እገዛ ብቁነት ሰንጠረዥ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 2022 የፌደራል ድህነት መመሪያዎች (FPG)<br>በቤተሰብ አባላት ብዛት መሰረት ለገንዘብ እገዛ ብቁ የሚሆን ያልተጣራ አመታዊ ወይንም ወርሀዊ ገቢ። | | | | | | |
| | 100% የ FPG | | 200% የ FPG | | 400% የ FPG | |
| የቤተሰብ አባላት ብዛት | አመታዊ ገቢ | ወርሀዊ ገቢ | አመታዊ ገቢ | ወርሀዊ ገቢ | አመታዊ ገቢ | ወርሀዊ ገቢ |
| 1 | $13,590 | $1,133 | $27,180 | $2,265 | $54,360 | $4,530 |
| 2 | $18,310 | $1,526 | $36,620 | $3,052 | $73,240 | $6,103 |
| 3 | $23,030 | $1,919 | $46,060 | $3,838 | $92,120 | $7,677 |
| 4 | $27,750 | $2,313 | $55,500 | $4,625 | $111,000 | $9,250 |
| 5 | $32,470 | $2,706 | $64,940 | $5,412 | $129,880 | $10,823 |
| 6 | $37,190 | $3,099 | $74,380 | $6,198 | $148,760 | $12,397 |
| 7 | $41,910 | $3,493 | $83,820 | $6,985 | $167,640 | $13,970 |
| 8 | $46,630 | $3,886 | $93,260 | $7,772 | $186,520 | $15,543 |
| *ከ 8 አባላት በላይ ላሉዋቸው ቤተሰቦች/ቤቶች : ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ሰው $4,720 ያክሉ።* | | | | | | |